# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 175 መስከረም 11 2004 ገጽ 1

**አዎ !!! አሁን ሁላችንም አንዱዓለም አራጌዎች፣ ሁላችንም እስክንድር ነጋዎች፤ ሁላችንም ደበበ እሸቱዎች፤ ሁላችንም ውብሸት ታዬዎች፣ ሁላችንም ርዕዮት ዓለሙዎች፣ ሁላችንም ስለሺ ሀጎሶች፣ ሁላችንም በቀለ ድሪባዎች፤ ሁላችንም አልባና ሌሊሳዎች ነን። አሁን ሁላችንም እስረኞች ነን። በቅርቡ ግን እስር ቤቶቻችንን ሰብረን ነፃ እንወጣለን!!!**

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ግንቦት 7 "ወያኔ በሽብርተኘነት ሥም ለነጻነትና ለዲሞክራሲ በሚታገሉ ዜጎች ላይ የከፈተው የእሥር ዘመቻ "የማይቀረውን ውድቀት ለማስቀረት የሚደረግ ከንቱ መፍጨርጨር ነው" ሲል መግለጫ አውጣ

ግንቦት 7 በመግለጫዉ፤ የፋሽስቱ መለስ ዜናዊ ቡድን ካለፈው ዱግሜ 2003 ዓ.ም ጀምሮ አገር ውስጥ ለፍትህ፤ ለ እኩልነትና ለዲሞክራሲ በሚታገሉ የሰላማዊ ትግል አራማጆች ላይ እየወሰደ ያለው የእስር እርምጃ በሰሜን አፍሪካና በመካከለኛ ምስራቅ የታየው የጸረ አምባገነኖች ህዝባዊ አብዮት በወያኔ ሠፈር የፈጠረው ሽብርና ድንጋጤን መግለጫ ነዉ በሏል።

የግንቦት 7 ለፍትህ ለ እኩልነትና ለነጻነት ንቅናቄ በዚሁ መግለጫዉ፤ ወያኔ እራሱ ተሸብሮ ሌሎችን በሽብርተኘነት የሚወነጅለው በዘረኝነት ላይ ከተመሰረተው ድርጅታዊ ባህሪው በመነጨ የፍርሃትና የጥርጣሬ ስነልቦና የተነሳ ነው ካለ በኋላ በማስከተል፤ ላለፉት 20 አመታት ዘረኛ የሆነ ድርጅታዊ መዋቅር በመላው አገሪቱ በመዘርጋት የፈጸማቸውን ወንጀሎችም ዘርዝሮአል።

የወያኔ ዘረኛ ገዥ ጉጅሌ ስልጣን ላይ ከወጣ ጀምሮ በሃገርና በህዝብ ላይ የፈጸመውን ግፍና ጭካኔ ከዘረኛ ማንነቱ ጋር አስተሳስረን ካላየነው በሚገባ ልንረዳው አንችልም ያለው የግንቦት7 መግለጫ ወያኔ ህዝብን በፍርሃት ድባብ ውስጥ ለመክተት ሽብርን እንደስልት እንደሚጠቀም በዚህም ምክንያት የሚሞቱ እናቶች፤ ህጻናትና አዛውንቶች ህይወት እንደማያሳዝነው ገልጾአል። የሥልጣን ዕድሜውን በሌሎች ድርጅቶች ኪሳራ እስከወዲያኛው ለማራዘም ሲባትን የኖረው የዘረኛው ወያኔ ጉጂሌ ቡድን ዜጎችን በፍርሃት ቆፈን ውስጥ ቀፍድዶ ለመግዛት ካለው ህልም የተነሳ ንጹሃን ዜጎች በተሰባሰቡበት ሰላማዊ ቦታዎች እራሱ ፈንጂ ቀብሮ ካፈነዳ በኋላ በተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች በተለይም በኦነግ ላይ ሲያላክክ እንደነበረ ከእኛ ከኢትዮጵያዊያን አልፎ የአሜሪካ መንግሥት ጭምር እንደሚያውቀው በቅርቡ በዊኪሊክስ በኩል ሾልኮ ለህዝብ እይታ የቀረበው ምስጥራዊ የአሜሪካ ዲፕሎማሲያዊ ሰነድ አጋልጦታል ብሎአል። እንዲህ አይነቱን እኩይ ተግባር የወያኔ ገዥ ጉጅሌ መፈጸም የተቻለው ከዘረኛነት ከሚመነጭ ጭካኔው እንደሆነ በመግለጫው ተጠቅሶአል። የወያኔን ገዥ ጉጅሌ ከዘረኛ እምነቱና አመለካከቱ ጋር በደንብ ካላየነው እስካሁን የፈጸማቸውን ጨካኝ ድርጊቶች በሚገባ መረዳት አንችልም፤ ወደፊት ሊፈጽማቸው የሚችላቸውንም ተመሳሳይ ድርጊቶች በሚገባ ተረድተን ራሳችንን ከጉጅሌው ጥቃት መከላከል አንችልም ብሎአል የግንቦት 7 መግለጫ።

በተመሳሳይ ዜና አንድነት ለፍትህና ለዲሞክራሲ መስከረም 5 2004 ዓ/ም በሰጠው መግለጫ ወያኔ እራሱ ተሸብሮ ህዝብ ማሸበሩን በአስቸኳይ እንዲያቆምና ለእንዲህ አይነት ስጋት የዳረገውን አምባገነንነት ባህሪዉን ተወት አድርጎ ለድርድር መቀመጥ ብቸኛ አማራጭ ነው ካለ ቦኋላ ይህ ዕድል ካመለጠ የወያኔ እንደፖለቲካ ድርጅት የመቀጠል ህልውና ጥያቄ ውስጥ ይገባል ሲል አስጠንቅቋል። የአንድነት ለፍትህና ዴሞክራሲ ፓርቲ፡ በ2004 የአዲስ አመት መልእክቱ፡ የኢትዮጵያ ህዝብ ልክ እንደ 1966ቱ አብዮት፡ የፖለቲካ ድርጅቶች እስኪቀሰቅሱት ሳይጠብቅ፡ የተነጠቀውን ነጻነት ለማስመለስ ባንድነት እንዲነሳ የትግል ማቅረቡም ይታወሳል።

የግንቦት 7 እና አለም አቀፍ የፖለቲካ ንቅናቄ ለዲሞክራሲያዊ ለውጥ በኢትዮጵያ ያወጡትን መግለጫ ሙሉ ቃል በገጽ 3 ይመልከቱ።

## ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ የጀመረው የጅምላ እስራት ዘመቻ ህዝባዊ ዓመፅ ማስነሳቱ እንደማይቀር ተገለጸ

ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሽብርተኝነት ስም በስፋት የጀመረውን እስራት በመቀጠል የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ አንዱዓለም አራጌን ጨምሮ አምስት የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮችንና ታዋቂውን ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ፤እንዲሁም በቀለ ገርባ፡ ኤልባና ሌሊሳና ዝነኛዉን ደበበ እሸቱንና ሌሎችንም በግፍ ማሰሩን ተከትሎ፣ ህዝባዊ አመጽ ሊነሳ እንደሚችል በአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ የሆኑ አስተያየት ሰጪዎች ገለጹ።

አረመኔው የወያኔ አገዛዝ በቁጥጥሩ ስር አውሎ እንደፈለገው በሚፈነጭባቸው የመገናኛ ብዙሃን ኢትዮጵያዊያኑ የታሰሩት ሲያሴሩት በነበረው የሽብር ወንጀል ምክንያት እንጂ፣ በፖለቲካ አቋማቸው ምክንያት አይደለም በማለት ሌት ከቀን ህዝብን በማደንቆር ላይ መሆኑን አስመልክቶ ዘጋቢያችን በአዲስ አበባ ከተማ የተለያዩ ክፍለ ከተሞች የሚገኙ ዜጎችን አነጋግሮ ባገኘው ምላሽ፣ ወያኔ አሁን የጀመረው አይን ያወጣ የንቀት ተግባር፣ ለዘመናት ተፈናጥጦበት ካለዉ የኢትዮጵያ ህዝብ ጫንቃ ላይ ማስወገጃ ምእራፍ የመጀመሪያው ነው ብለዋል።

ዘጋቢያችን በአዲስ አበባ በተለያዩ ክ/ከተማ የሚኖሩና ስማቸው እንዳይገለጽ የጠየቁ አዛውንትንና አንድ ወጣትን አነጋግሮ በሰጡት ምላሽ፣ ስለ (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ በተቃዋሚዎች ላይ በጸረ ሽብርተኛነት ስም የሚያካሂደዉን የ እስር ዘመቻ በመቃወም አለም አቀፍ የሰበአዊ መብት ተሚጋች ድርጅቶችና ኢትዮጵያዊያን የሲቪክ ማህበራት መግለጫ አወጡ

ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ የመጣው የህዝብ ብሶት ወደ አመጽ ይሸጋገራል የሚል ፍርሃትና ድንጋጤ ያናወጠው የህወሃት ዘረኛ ቡድን ከስጋት በመነጨ ስሜት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የጀመረውን የእስር ዘመቻ በመቃወም የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች፤ የስቪክና አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ተሚጋቾች የሚያወጡት የውግዘት መግለጫ እንደቀጠለ ነዉ።

አዲሱን የወያኔ የዕስር ዘመቻ በመቃወም ሰሞኑን መግለጫ ያወጡ ታዋቂዎቹ የአለም አቀፉ የሰብአዊ መብት ተሚጋች ድርጅቶች **1ኛ** አምንስቲ ኢንተርናሽናል፤ **2ኛ** ሂውማን ራይትስ ወች፤ **3ኛ** ሪፖርተርስ ዊዝአዉት ቦርደርስ፤ **4ኛ** አለም አቀፍ የጋዝጠኞች ጥበቃ ኮሚቴና **5ኛ** የኢትዮዲያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ **6ኛ** ዓለምአቀፍ የሲቪልና ፖለቲካዊ ንቅናቄ ለዴሞክራሲያዊ ለውጥ በኢትዮጵያ ናቸዉ።

አመነስቲ ኢነተርናሽናልና ሂውማን ራይትስ ወች በየግላቸው ባወጡት በዚህ መግለጫቸው የወያኔዉ አገዛዝ በዜጎች ላይ የከፈተው የእሥር ዘመቻ እየተካሄደ ያለው በአገዛዙ ላይ የሠላ ትችት የሚያቀርቡትን ጋዜጤኞችና ተቃዋሚዎች ኢላማ በማድረግ እንደሆነ ጠቅሰው ይህ እየተፈጸመ ያለው የፖለቲካ ባላንጣን ለማጥፋት እንደተፈለገ ለመተርጎም በሚቻለው የፀረ_ሽብርተኝነት ህግ ተብዬውን አዋጅ በመጠቀም እንደሆነና ይህ ደግሞ አዋጁ ከመጽደቁ በፊት ተሰግቶ እንደነበረው የዘጎችን ሃሳባቸውን በነጻነት የመግለጽ መብት የሚጋፋ መሆኑን አስመስክሮአል ብለዋል። በማያያዝም አገዛዙ በቅርቡ ከ መጋቢተ ወር ወዲህ እንኳን በትንሹ ወደ 100 ኢትዮዲያዊያን የተቃዋሚ ፓርቲ አባላትንና 5 ጋዝጠኞችን መያዛቸዉንና ሁሉም በሚገርም ሁኔታ በአሸባሪነት መከሰሳቸዉም አስገራሚ መሆኑንም ጠቁመሙአል።

የአመነስቲ ኢነተርናሽናል ማህበር ያፍሪካ ም\ዳይሬክተር Michelle Kagari*ሚኬል ካጋሪ፤ የኢትዮዲያ መንግስት የተቃዋሚ ፓርቲዎችነም ሆነ ያክቲቪስቶችን እንዲሁመ የጋዝጠኞችን ጠንካራ ትችት ና ሀሳብ መቋቋም ወይም መቀበል ካለምቻል በፀረ-ሽብርተኝነት ስም አፍኖ ዝም ለማስኘት እየተንቀሳቀሰ ነዉ ብለዋል። ሲያብራሩም ይህ ሁሉ እስረኛ የተቃዋሚ ፓርቲ አባል፣ ጋዜጠኛ ና አክቲቪሰቶች በሙሉ ባንድ ጊዜ ባሽባሪነት ተግባር ላይ ተሰመርቷል ማለት በጭራሽ የማይመስልና የማያሳምንም ነዉ ብለዋል። ይህ የሚያሳየዉ ይላሉ ወየዘሮዋ፡ አገዛዙ የተለያዩ የፖለቲካ ጥያቄዎችን በማንሳት ህጋዊና ሰላማዊ ተቃዉሞ የሚያደርግን ማንም ይሁን ማን በማሳደድ ና በማሰር ሌሎችንም ዝም ለማሰኘት ዝም የማይሉም ከሆነ ወከባዉ እኔን ያየህ ተቀጣ አዘል መልእክት እንዲኖረው ነዉ ብለዋል።(ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## ከራሱ በቀር በጀሌዎቹ ላይ እምነት የሌለው ህወሃት በብአዴን አመራር አባላት ላይ ግምገማ ማድረግ መጀመሩ ታወቀ። የግምገማው ዋንኛ ትኩረት የፖለቲካ ታማኝነት ላይ ያነጣጠረ ነው ተብሎአል

የራሱን ጥላ እስከመጠራጠር የደረሰውና እንደቆሰለ አውሬ ያገኘውን ሁሉ እየነከሰ ያለው ዘረኛና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ሰሞኑን በብአዴን አመራር አካላት ላይ የርስ በርስ ግምገማ እንዲካሄድ በማዘዙ አባላቱ ርስ በርስ በዝግ ስብሰባ እየተገማገሙና እየተከፋፈሉ እንደሆነ የውስጥ ምንጮቹን ዋቢ በማድረግ ዘጋቢያችን ከባህር ዳር ባስተላለፈልን ዘገባ አመለከተ።

እንደ ዘጋቢያችን ሪፖርት ይህ ያሁኑ የብአዴን የግምገማ ዋና አላማ ነባር አባላቱን በአዳዲስ አባላት ለመተካት በሚል ሽፋን ሲሆን ፣ ከበስተጀርባ ያለው ድብቅ አጀንዳ ግን የወያኔውን ህዋሃት አገዛዝ የበላይነት የማይቀበሉና የመቃወም አዝማሚያ ያሳዩ ነባር አባላትን ለመመንጠር እንደሆነ ታውቁአል። ተያይዞ የደረሰን ዘገባ እንደሚያመለክተው፣ በአዲሶቹና በነባሮቹ የብአዴን አመራር አካላት መካከል በሚካሄደው ግምገማ ነፍስ እስከመጠፋፋት መደረሱን ለማወቅ ተችሎአል።

በዚህም መሰረት በአማራ ክልል ውስጥ በሚገኘው የደቡብ ወሎ ወግዲ ወረዳ የሚገኙ የብአዴን ምክር ቤት አባላት እረስ በርስ በሚገማገሙበት ወቅት ስሜታቸውን መቆጣጠር ተስኖአቸው በሽጉጥ መገዳደላቸውን የራሱ የወያኔው ኢህአዴግ ምንጬች መግለጻቸውን ዘጋቢያችን አክሎ አሳዉቋል።

በተመሳሳይ መልኩ ይሄው ግምገማ ተብየ እየተካሄደባቸው ባሉት የአማራ ክልል የተለያዩ ወረዳዎች በርካታ በህዋሃት የበላይነትና አምባገነንነት ደስተኛ ያልሆኑ የብአዴን አባላት፣ አመራሮቻቸውን በስሜት እስከመዝለፍ መድረሳቸውን ለማወቅ ተችሎአል።

ዘጋቢያችን ምንጮቹን ዋቢ በማድረግ ከላከልን ሪፖርት ለመረዳት እንደቻልነው አንዳንዱ ግምገማ እንደ ልጆች ጨዋታ እጅግ የሚያስገርም መሆኑንና፣ በአንድ ወቅት የተነገረ ቀልድ ሳይቀር እየተነሳ "ምን ለማለት ፈልገህ ነው? ፈልገሽ ነው? "እየተባባሉ ቃላቶቻቸውን በመመንዘር አባላቱን የማስጨነቅ ስራ እየተሰራ ነው" ማለታቸው ታውቁአል።

ዘጋቢያችን አንድ በደሴ ከተማ የሚኖሩ ስማቸው እንዳይጠቀስ (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

# ርእሰ አንቀጽ

የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 175 መስከረም 11 2004 ገጽ

## ሁላችንም አንዱዓለም አራጌዎች ነን!!!

ዛሬ የምንገኝበት እውነታን አቶ አንዱዓለም አራጌ በመለስ ዜናዊ ችሎት በተናገራቸው ሁለት ዓረፍተ ነገሮች አጠቃሎታል፤ እንዲህ በማለት።

*ለመጀመርያና ለመጨረሻ ጊዜ የምለው አለኝ፤ በኢትዮጵያ የተያዘው ነገር የፖለቲካ ተቃውሞ አፈና ስለሆነ ፍርድ ቤቱ እስከ ሞት ድረስ መወሰን ይችላል:: ከዚህ በኋላ ምንም ነገር አልናገርም።*

በመለስ ዜናዊ ዘረኛና አፋኝ ህግ መሠረት ህጋዊና ሰላማዊ ትግል በሽብርተኝነት ያስከስሳል። አቶ አንዱዓለም እንዳለውም ለዚህ ችሎት ሃቅን መናገር ፋይዳ የለውም። ከዚህ በፊት በተደጋጋሚ እንደታየው በችሎት ላይ የተቀመጡ “ዳኞች” እንደማገኛውም ሰው “ለፍ/ቤቱ” ውሳኔዎች እንግዶች ናቸው። ስለሆነም ችሎቱ ላይ ለተቀመጡ ግዑዛን ፍጥረቶች ማብራሪያ መስጠት - ሰሙም አልሰሙም - በሚያነቡት ውሳኔ ላይ የሚያመጣው ለውጥ የለም። በዚሁ ሁሉ ምክንያት እችሎት ተብዬው ውስጥ መከራከር ዋጋ የለውም።

ከዚህ በፊት አንድ ታዋቂ ኢትዮጵያዊ ከሰው የሰማሁት ቀልድ ነው ብለው የሚከተለውን ተናግረው ነበር።

*የኢትዮጵያ ሕዝብ በሦስት ይከፈላል - ታስረው የተፈቱ፣ የታሰሩ እና ወደፊት የሚታሰሩ*

ከላይ የተባለው ቀልድ ነው። እውነታው ግን ሁላችንም የታሰርን መሆናችን ነው። ዛሬ ሁላችንም አንዱዓለም አራጌዎች፣ ሁላችንም እስክንድር ነጋዎች፤ ሁላችንም ደበበ እሸቱዎች፤ ሁላችንም ውብሸት ታዬዎች፣ ሁላችንም ርዕዮት ዓለሙዎች፣ ሁላችንም ስለሺ ሀጎሶች፣ ሁላችንም በቀለ ድሪባዎች፤ ሁላችንም ኦልባና ሌሊሳዎች ነን። ዛሬ እያንዳንዳችን በኢትዮጵያ እርስ ቤቶች ከሚማቀቁ ወገኖቻችን እንደ አንዱ ወይም እንደ አንዷ ነን። ሁላችንም እስረኞች ነን።

ከፊት ለፊታችን የተደቀነውም ጥያቄ እንዲህ የሚል ነው።

*ለመሆኑ የታሰርንበትን እስር ቤት ሰብረን ለመውጣት ዝግጁዎች ነን? ... .... ወይም በእስር ለመማቀቅ ፈቅደናል?*

አሳሪዎቻችን ጥቂቶች መሆናቸውን እናውቃለን። እኛ ታሳሪዎቹ ግን ብዙሃን መሆናችንን የታወቀ ጉዳይ ነው። እንደምን ጥቂቶች ብዙሃንን አስረው እንዲንደላቀቁ እንፈቅዳለን?

የታሰርንበት ወህኒ ቤት የበሰበሰና ገፋ ቢደረግ የሚደረመስ መሆኑን እናውቃለን። የብረት አጥር ይመስሉ የነበሩ የቱኒዚያ፣ የግብጽና የሊቢያ እስር ቤቶችም ተደምስው ህዝቦቻቸው የነፃነት አየር መተንፈስ መጀመራቸውን አይተናል። እናስ የታሰርንበትን አሮጌ እስር ቤት የመደርመስ አቅም እንዴት እናጣለን?

ቆርጠናል። ሁላችንንም እንደ አቶ አንዱዓለም አራጌ መሮናል። ነፃነት ዋጋ እንደሚያስከፍል እናውቃለን። የነፃነት ዋጋ ህይወትም ሊጨምር እንደሚችል እናውቃለን። ነፃነታችን የሚጠይቀንን ዋጋ ለመክፈል ደግሞ ዝግጁዎች ነን።

የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ መወገድ ይኖርበታል። የመለስን አገዛዝ በቶሎ መላቀቅ፤ አዲሲቷን ውብ ኢትዮጵያን በቶሎ ያስገኝልናል።

በ2004 ዓ.ም. ይህ መልካም አጋጣሚ እንዲያመልጠን አንሻም። በዚህ ዓመት እስር ቤቶቻችንን ሰባብረን በመውጣት የነፃነት አየር መተንፈስ እንፈልጋለን፤ ለዚህም ተነስተናል።

አዎ !!! አሁን ሁላችንም አንዱዓለም አራጌዎች፣ ሁላችንም እስክንድር ነጋዎች፤ ሁላችንም ደበበ እሸቱዎች፤ ሁላችንም ውብሸት ታዬዎች፣ ሁላችንም ርዕዮት ዓለሙዎች፣ ሁላችንም ስለሺ ሀጎሶች፣ ሁላችንም በቀለ ድሪባዎች፤ ሁላችንም ኦልባና ሌሊሳዎች ነን። አሁን ሁላችንም እስረኞች ነን። በቅርቡ ግን እስር ቤቶቻችንን ሰብረን ነፃ እንወጣለን!!!

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●

## ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ በተቃዋሚዎች ላይ በጸረ ሽብርተኛነት ስም የሚያካሂደዉን የ እስር ዘመቻ በመቃወም . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

በመጨረሻም የዚህ እንድምታ ያገዛዙ ባለስልጣናተ በሀገሪቱ ባሁኑ ሰዓት በእንጥፍጣፊ የቀረችዉን ሃሳብን የመግለጽና የመናገር መብትን ከናካቴዉ ለያጠፏት ተግተዉ በመስራት ላይ መሆናቸዉን ነዉ ሲሉ ገልፀዋል።

በተመሳሳይ ሪፖርተርስ ዊዝአዉት ቦርደርስ የተባለውም ተቁአም በመስከረም 10 2004፣ የጸረ ሽብሩ ህግ በሚዲያዉና ሀሳብን በነጻ የመግለጽ ሰብአዊ መብት ላይ የተጋረጠ አደጋ ሆኑአል ሲል ጋዝጣዊ መግለጫ አዉጥቱአል። በመግለጫዉም ከአሜሪካዉ የመስከረም 11 የሽብር አደጋ ጀምሮ አንዳንድ መንግስታት የጸረ_ሽብርተኝነት ህግ ማዉጣታቸዉን አዉስቶ ግን እነዚህ አገዛዞች በሀገር ደህንነት ስም ነጻዉን ሚዲያና ሀሳብን በነጻነት የመግለጽን ሰብአዊ መብትን ለማፈኛ እየተጠቀሙበት መሆኑን ገልፆአል። በማያያዝም የኢትዮጲያዉ የጸረ_ሽብር አዋጁ ደግሞ ከዜጎች አልፎ የዉጭ አገር ጋዜጠኞችንም ባሸባሪነት ለማሳሰርም የመብቃቱን 2ቱን በእስር የሚገኙትን የስዊድን ጋዝጠኞችን በመጥቀስ አሳሳቢነቱን በመግለጫዉ አሳዉቆአል።

የኢትዮጲያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴም “ጸረ- ሽብር ወይስ ጸረ- ነጻ ፕሬስ” በሚል ባወጣዉ መግለጫ ዘረኛዉና አምባገነኑ መለስ ዜናዊ ያወጣውን የፀረ - ሽብር አዋጅ ጋዜጠኞችን፣ ፖለቲከኞችንና ባጠቃላይም የኢትዮጲያን ህዝብ ረግጦ ለመግዣ እየተጠቀመበት ነዉ ብሎአል።

ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ የጀመረውን የ እስር ዘመቻ በመቃወም መግለጫ ያወጡት እነኚህ አምስቱም ድርጅቶች ላለፉት በርካታ አመታት ወያኔ በዜጎቻችን ላይ የፈጸማቸውን ስቃያና እንግልት በመከታተል ሲዘግቡ የነበሩና የወያኔን ምንነት ለአለም አቀፍ ህብረተሰብ ያጋለጡ መሆናቸው ይታወቃል። ዓለምአቀፍ የሲቪልና ፖለቲካ ንቅናቄ ለዴሞክራሲያዊ ለውጥ በኢትዮጵያ የተባለዉ ድርጅት በበኩሉ ዕሁድ መስከረም 7/2004 “የኢትዮጵያ ሕዝብ የስልጣን ባለቤት ይሆናል!!” በሚል ርዕስ ባወጣው መግለጫ ጎሳን መሰረት ያደረገው የሕወሀት/ኢህአዴግ ማፊያና ቅጥረኛ ቡድን፡በሀገሪቱና ብሎም በህዝቡ ላይ ያደረሰዉንና እያደረሰ ያለዉን በሀገሪቱ ታሪክ ታይቶ የማይታወቅ የሰብአዊ መብት ጥሰትንና መንግስታዊ ሽብርተኝነትን በጽኑ እንደሚቃወም በመግለጽ ህዝቡ ይህንን የወያኔ አስከፊ ጭቆና ከላዩ ላይ አሽቀንጥሮ ለመጣል ለሚደረገው ትግል በአስቸኳይ እንዲነሳ የትግል ጥሪ አቅርቧል።

በዚህ መሠረት የስቪክ ድርጅቱ የአንድነት ለፍትህና ዴሞክራሲ ፓርቲ ያስተላለፈዉን የአድስ አመት የነፃነት የትግል ጥሪ መልእክት እንደሚጋራ እንዲሁም በሀገር ቤት የሚደረጉ የተቃውሞ ሰልፎችን ሙሉ በሙሉ እንደሚደግፍና ኢትዮጵያዊያን በሚኖሩባቸው ዋና ዋና የሰሜን አሜሪካና የአውሮፓ ከተሞችም ተመሳሳይ የተቃውሞ ሰልፎችን ለማድረግ እንደወሰነ ገልጾ፤ የአሜሪካና የካናዳ መንግስታት ከህወሀት/ኢ.ህአዴግ አምባገነንና ህገ-ወጥ አገዛዝ ጋር ያላቸውን የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ እንዲቀይሩ፤ የህወሀት\መለስ ዘረኛ አመራሮች፡በፈፀሙት የዘር ማጥፋት ወንጀል አለምአቀፉ የወንጀል ፍርድቤት እንዲቀርቡ ጫና እንዲያደርጉ፤ በመላው አገሪቱ የሚገኙ የፖለቲካ እስረኞች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲፈቱ፤ በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጪ ያሉ ኢትዮጵያዊያን፡ የህወሀት/ ኢ.ህአዴግን አመራርና ቅጥረኛ አባላትን እንዲያገሉ፤ በውጪ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን የህወሀት/ኢ.ህአዴግ ኤምባሲን አገልግሎት እንዳይጠቀሙ፤ ከሕወሀት ጋር የተዛመዱ የንግድ ድርጅቶችን፡ የአምልኮ ቦታዎችን፡ ማህበራትና ተቋማትን መገልገል እንዲያቆሙም ጥሪ አቅርቧል።

በመቀጠልም የኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባናል የሚሉ ድርጅቶች ሁሉ የተጋረጠባቸውን መሰናክል አስተውለው ሁሉን አቀፍና የነጻነት ትግሉን ከግብ ሊያደርስ የሚችል እንዲሁም አገሪቱን ለብሄራዊ እርቅና ለሰላም፡ ለነጻና ፍትሀዊ ምርጫ የሚያሰናዳና የአገሪቱን ፖለቲካዊና ግዛታዉ ሉአላዊነት ወደሚያስከብር የአደራ መንግስት የሚወስድ፡ ጊዜያዊ ብሄራዊ ምክር ቤት ወይም ሸንጎ (National Council) እንዲያቋቁሙ አሳስቧል።

በማጠቃለልም የህወሀትን ዘረኛ አስተዳደር አስወግዶ በምትኩ ሰላምን፣ብልጽግናንና ነጻነትን ማስፈን የሚችል ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመመሥረት በሚደረገው ትግል ላይ፡ ሁሉም የዴሞክራሲ ሀይሎች እንዲተባበሩ፡ የትግል ጥሪዉን ለሁሉም ኢትዮጲያዊ አቅርቧል።

በተያያዜ ዜና ለፊታችን መስከረም 21 ቀን አዲስ አበባ በሚገኘው መስቀል አደባባይ ላይ ሠላማዊ የተቃውሞ ሠልፍ የጠሩት ሁለቱ ድርጅቶች አስከዛሬ ከወያኔ የአዲስ አበባ ጽቤት ፈቃድ የሚሰጥም ሆነ የሚከለክል ነገር ባይሰሙም የጠሩትን ሰልፍ ለማካሄድ በከፍተኛ እንቅስቃሴ ላይ መሆናቸውን የኢትዮጵያ ሳታላይት ቴለቪዥን ዘግቦታል። እንደሰላማዊ ሰልፉ አስተባባሪዎች መግለጫ ወያኔ ሠላማዊ ሥልፉን ለመከልከል የሚያስችለው ምንም አይነት ህጋዊ መስፈርት የለም መባሉን ኢሳት አዘጋጆቹን ጠቅሶ ዘግቦአል። የመግለጫውን ሙሉ ቃል በገጽ 4 ይመልከቱ።

## ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ የጀመረው የጅምላ እስራት . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ወያኔ ተግባርም ሆነ በኢትዮጵያዊያን ላይ እየፈጸመ ስላለው በደል ማውሪያው ጊዜ አልፉአል። ግፍና በደሉ ሞልቶ እስኪተርፍ ድረስ የሚፈልገውን አረመኔያዊ የሆነና ሰይጣናዊ ተግባሮቹን ሁሉ ፈጽሙአል፣ አሁንም እየፈጸመ ነው። ይህ ሁሉ ድርጊቱ ኢትዮጵያዊያን በፍርሃት ውስጥ እንዲገቡና ሰጥ ለጥ ብለው እንዲገዙ ካለው ከንቱ ምኞት የተነሳ ነው። ይሁን እንጂ የኢትዮጵያዊያንን ባህሪ ያላወቀውና የማያውቀው ወያኔ አንድ ቀን ማንነታችንን የሚረዳበት ጊዜ ተቃርቧል የዚህም ጊዜ ጅማሮ የነኝህ ውድ ኢትዮጵያዊያን ወደ እስር ቤት መግባት ሊሆን ይችላል ምን እንደምናደርግም በቅርቡ ወያኔ በአይኑ ይመለከታል ብለወል።

ዘረኛውና አምባገእነኑ የወያኔ አገዛዝ በተለይም በምርጫ 97 ወቅት በኢትዮጵያዊያን የደረሰበትን ሽንፈት ለማካካስና አንፈልግህም ያለውንም ህዝብ ለመበቀል ተከታታይ የሆኑ ዘርፈ ብዙ ሽብሮችን ሲፈጽም መቆየቱን፣ ሰበብ አስባብ በመፈለግ ንጹህ ኢትዮጵያዊያንን በጂምላ ወደ ተለያዩ እስር ቤቶች በማጎር ላይ መሆኑን በተደጋጋሚ ስንዘግብ መቆየታችን ይታወሳል።

በግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን
የፖስታ ሳጥን ቁጥር :- POBox: 4916 2003EX Haarlem, The Netherlands

## የማይቀረውን ውድቀት ለማስቀረት ከንቱ መፍጨርጨር

ከግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የተሰጠ መግለጫ መስከረም 9 2004

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የትግራይ ነጻ አውጭ ድርጅት የሚል ስያሜ ይዞ ከሰማኒያ በላይ ብሄረሰቦች ያሉባትን ሃገር ይገዛል። የትግራይ ነጻ አውጭ የሚል ስም ይዞ በኢትዮጵያ ስም አለም አቀፍ ውል ይዋዋላል። አለም አቀፍ ብድር ይወስዳል። የትግራይ ነጻ አውጭ የሚል ስም እንደያዘ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኘውን መሬት በሙሉ ባለቤት ሆኗል። የትግራይ ነጻ አውጭ የሚል ስም ይዞ የሃገሪቱን ገበሬ በሙሉ በጭሰኛነት ይገዛል። የትግራይ ነጻ አውጭ የሚል ስም እንደያዘ የኢትዮጵያን ለም መሬቶች ለባእዳን ይሸጣል። የትግራይ ነጻ አውጭ የሚል ስም ይዞ በሌሎች ክልሎች የሚገኙ የወርቅና የሌሎች ማእድኖች ባለቤት ሆኗል። የትግራይ ነጻ አውጭ የሚል ስም ይዞ የሃገሪቱን የአስመጪነትና ላኪነት ንግድ ተቆጣጥሯል። በመላው ሃገሪቱ የንግድ፣ የባንክ፣ የኢንዱስትሪ የትራንስፖርት የኢንሹራንስ የኤኮኖሚ ዘርፎች ብቸኛው ባለሃብት ሆኗል። የሆቴሎች የፋብሪካዎች ዋናው ባለቤት ሆኖ የኢትዮጵያን ላብአደር ከባርነት ልዩነት በሌለው ደሞዝና የቅጥር ውል ያሰራል። የትግራይ ነጻ አውጭ የሚል ስም ይዞ የተለያዩ ክልሎችን ይገዛል። የሃገሪቱን የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ኮምሽኖች፣ ትልቅና አነስተኛ ጥቅም የሚገኝባቸው ተቋማት አዛዥ ሆኗል። የትግራይ ነጻ አውጭ የሚል ስም ይዞ የኢትዮጵያን ኤምባሲዎች ተቆጣጥሯል። የትግራይ ነጻ አውጭ የሚል ስም ይዞ የኢትዮጵያን መከላከያ ሃይል መቶ በመቶ ተቆጣጥሯል። የትግራይ ነጻ አውጭ የሚል ስም ይዞ የኢትዮጵያን የደህነነትና የፖሊስ ሃይል ለብቻው ያዛል።

ዛሬ ሃገራችን የገባችበት ፈተና ራሱን የትግራይ ነጻ አውጭ በሚል ስም ሰይሞ የራሱን የአናሳ ጠባብ ጥቅምና ፍላጎት በመላው የሃገሪቱ ህዝብ ኪሳራ ለማስፈጸም ቆርጦ በተነሳ ዘረኛ ገዥ ጉጅሌ አገዛዝ ስር መውደቋ ነው። ጠባብና ዘረኛ አመለካከት ይዞ ስለኢትዮጵያ ህዝብ በረሃብ ማለቅ ማሰብ የማይቻል ነው። ጠባብና ዘረኛ አመለከከት ያለው የትግራይ ገዥ ጉጅሌ ሃገራዊ ውርደት፣ ሊሰማው አይችልም። የሃገሪቱ ትውልድ ተስፋው ቢጨልም፣ የሃገሪቱ የተፈጥሮ ሃብት ቢወድም ጉዳዩ አይደለም። የወያኔ ገዥ ጉጅሌ ዘረኛነት፣ ልክ በሌሎች የአለማችን ክፍሎች እንደታዩት ዘረኛነቶች በዘር መነጽር እያየ የጉጅሌ አካል ነው ከሚለው ክፍል ውጭ ከሚገኘው ሰፊው የሃገሪቱ ማህበረሰብና ዜጋ ጋር የሚያገናኘው የስብእና ክር የለም። የትግራይ ነጻ አውጭ ድርጅት የኢትዮጵያ ህጻናት በጠኔ ቢያልቁ፣ የኢትዮጵያ ወጣቶች ሃገራቸውን ጥለው ሲሸሹ በረሃና ባህር በልቷቸው ቢቀር፣ እህቶችና እናቶች በሃገር ውስጥና በውጭ ሃገራት ባለግዜ ባለጌዎች ቢደፈሩ፣ አረጋውያን ከመከራ የተረፈች ቀሪ ህይወታቸውን በጠኔ በበሽታና በወህኒና በስቃይ ቢያሳልፉ ደንታው አይደለም። የትግራይ ነጻ አውጭ ድርጅት ነውና።

በወያኔ ዘረኛ የጭካኔ መነጽር ሲታይ አንድ አፍ ያልፈታ፣ ገና ዳዴ ማለት ያልቻለ ህጻን ታዳጊ ጠላት እንጂ፣ እንክብካቤ የሚሻ፣ የሚሳሳለት ፍጡር አይደለም። አረጋውያንም ሊዋረዱ የሚገባቸው የጠላት አባቶችና እናቶች እንጂ ድጋፍ የሚሹ አቅመ ደካሞች አይደሉም። ሃገር ለጠባብ ዘረኛ ጥቅም የምትመዘበርና የምትዘረፍ ጎተራ እንጂ የሁሉም ዜጋ መሰባሰቢያ የክብርና የኩራት ምድር አይደለችም።

የወያኔ ዘረኛ ገዥ ጉጅሌ ስልጣን ላይ ከወጣ ጀምሮ በሃገርና በህዝብ ላይ የፈጸመውን ግፍና ጭካኔ ከዘረኛ ጉጅሌ ማንነቱ ጋር አስተሳስረን ካላየነው በሚገባ ልንረዳው አንችልም። ወያኔ በቅርቡ ከዊኪሊክስ መረጃ እንዳየነው ራሱ ፈንጅ ቀብሮ፣ የሃገሪቱን ዜጎች ገድሎ ሲያበቃ በተቃዋሚዎች ላይ የሚያላክክ እኩይ ቡድን ነው። ይህን አይነቱን እኩይ ተግባር የወያኔ ገዥ ጉጅሌ መፈጸም የተቻለው ከዘረኛነት ከሚመነጭ ጭካኔው ነው። የወያኔን ገዥ ጉጅሌ ከዘረኛ እምነቱና አመለካከቱ ጋር በደንብ ካላየነው እስካሁን የፈጸማቸው ጨካኝ ድርጊቶችን በሚገባ መረዳት አንችልም። ወደፊት ሊፈጽማቸው የሚችላቸውን ተመሳሳይ ድርጊቶች በሚገባ ተረድተን ራሳችንን ከጉጅሌው ጥቃት መከላከል አንችልም።

ውሃና ዘይት እንደማይቀላቀሉ ሁሉ ዘረኛነትና ዲሞክራሲ፣ ዘረኛነትና የህግ የበላይነት፣ ዘረኛነትና እኩልነት፣ ዘረኛነትና አርቆ አሳቢነት፣ ዘረኛነትና ሆደሰፊነት፣ ዘረኛነትና መብት አክባሪነት፣ ዘረኛነትና ለሁሉም የአንድ ሃገር ዜጎችና ማህበረሰቦች ተቆርቋሪነት አብረው አይሄዱም።

ዘረኛነት በመሰረተ ባህርዩ ራሱ ከሽብር ጠርዝ ላይ የቆመ የአእምሮ ቅላጼ ነው። ዘረኛነት ዙሪያው ሁሉ ገደል፣ ከበባና ጥቃት ብቻ ሆኖ የሚታየው በፍርሃት ከተሞላ ቦቅቧቃ ህሊና ጋር የተቋራኘ ነው። እንደ ወያኔ ደግሞ ዘረኛ በሆነ መንገድ ተደራጅቶ፣ ሃገር መዝረፍ፣ በሃገር ብሄራዊ ጥቅምና ደህንነት ላይ ወንጀል መፈጸም፣ ህዝብን ማዋራድና ማሰቃየት ስራው አድርጎ የኖረ ድርጅት ዙሪያውን የሚታየው ገደል ከሲኦል የጎደጎደ፣ ሳር ቅጠሉና የራሱ ጥላ ሳይቀር ጠላት ሆኖ እንደሚታየው ማወቅ አለብን። የወያኔ ዘረኛ ጉጅሌ ህዝብን የማሸበር ድርጊት መነሻው ራሳቸውን በራሳቸው በማሸበር እነዚህ ዘረኛ አካላት የፈጠሩት የተሸበረ ማንነታቸው ነው። የግንቦት 7 ንቅናቄ ከተመሰረበት ቀን ጀምሮ እንቅልፍ የነሳቸው ድርጅት የሆነው በደንባራው ዘረኛ ህሊናቸው ላይ የተደመረ የነጻነት የፍትህና የእኩልነት ቃጭል ስለሆነ ነው።

ለወያኔ ዘረኛ ጉጅሌ አላፊ አግዳሚው ሰማዩና ምድሩ ግንቦት ሰባት ነው። ግንቦት ሰባት የሚባል ድርጅት መኖሩን ከማያውቁ ግለሰቦች አንስቶ በቅርቡ ከግንቦት ሰባት ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የሌላቸው የአንድነት ፓርቲ ምክትል ሊቀመንበር አንዷለም አራጌንና ሌሎች የፓርቲውን የምክር ቤት አባላትና እውቁን ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ከግንቦት 7 ጋር አሲረዋል በሚል የሃሰት ክስ መስርቶ የወያኔ ዘረኛ ገዥ ጉጅሌ ወደ ወህኒ እንዲረውራቸው ያስደረገው በጁ መረጃ ኖሮት ሳይሆን በፍርሃትና በከበባ የተወጠረው ጭንቀቱ ነው። ዘረኛነት ሰው ለመክሰስና ለማሰር መረጃ አያስፈልገውም። ዘረኛነት እውነትን ለመደፍጠጥ ሃሰትን ለማንገስ ይሉኝታ አያስፈራውም። ዘረኛነት ከአመክኖ ጋር አይገናኝም። በዘረኛነት ለተለከፈ የወያኔ ገዥ ጉጅሌ አእምሮ ስልጡን ክርክርና ውይይት የሚባል ነገር ባእድ ነው።

ዘረኛነት ላሳበደው የወያኔ ገዥ ጉጅሌ፣ የኢዮጵያን ህዝብ እስከአጥንቱ በመጋጥ መዝረፍ፣ የኢትዮጵያን ህዝብ የዘረኛው ጉጅሌ ገረድ፣ አሽከር ተላላኪ ዘበኛ አድርጎ ማየት፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ብርቅና ድንቅ እንዲሁም ክቡርና ቅዱስ አድርጎ የሚያያቸውን እምነቶቹንና እሴቶችን ማራከስ የደስታና የእርካታ ምንጭ ነው። የዘረኛነት ዛር ምሱ የሌሎችን ሲቃ ማዳመጥ፣ የሌሎችን ውርደት መመልከት ነው።

ሰሞኑን ወያኔ የተያያዘውን ሰላማዊ ሰዎችን በሽብር ስም የማሸበር፣ ሰላማዊና ህጋዊ የፖለቲካ ተቃዋሚዎችንና ጋዜጠኞችን በሽብር ስም እያፈሰ በየእስር ቤቱ የማጎር ድፍረቱና ጨካኝነቱ የመነጨው ከዘረኛነቱ ነው። በእጃቸው ስንጥር ያልያዙ ሰዎችን አሸባሪዎች በማለት በወታደር ከቦ በህጻናት ልጆቻቸው፣ በወላጆጃቸውና በሚያከብራቸው ወገናቸው ፊት በካቴና አስሮ እየጎተቱ መውሰድ የሚቻለው፣ ታሳሪዎቹንና ልጆቻቸውን፣ ቤተሰቦቻቸውን ሊዋረዱና ሊሰቃዩ የሚገባቸው አይጦች ናቸው ብሎ በማሰብ የሚሰራ እኩይ ስራ ነው። ወያኔ ያለምንም ይሉኝታ አይንኑ በጨው ታጥቦ፣ ፍርድ ቤቶችን የሃሰት ክስ መመስረቻ፣ መገናኛ ብዙሃኑን የሃሰት ወንጀል ማሰራጫ ማድረግ የሚቻለው ጭፍን ዘረኛነት የደፈነው ህሊና ባላቸው እብሪተኛ ገዥዎች የተሞላ ስለሆነ ነው።

ከሰሞኑ የዘረኛው የወያኔ ገዥ ጉጅሌ ቅጥ ያጣ መቅበዝበዝ የሚያሳየው፣ ይህ ዘረኛ ቡድን ለሽህ አመት ይዘልቃል ብሎ ያሰበው ዘረኛው አገዛዙ በወራት ውልቅልቁ ሊወጣ የሚችልበት ሁኔታ እንዳለ እየተረዳ መምጣቱን ነው። የመካከለኛው ምስራቅና የሰሜን አፍሪቃ ህዝባዊ አመጽ አይነካኝም እያለ ራሱን ሲሸነግል የከረመው ዘረኛ ጉጅሌ በኢትዮጵያ ውስጥ የተረገዘው የህዝብ ቁጣ የቱኒዝያንና የግብጽን ቁጣ የልጆች ጫዋታ የሚያስመስል ግዙፍ ቁጣ እንደሆነ እየታየው ነው። ጥቂት የገዥው ጉጅሌ አባላት በጥጋብ ቁንጣን ሲቁነጠነጡ፣ ገጠሩና ከተማው በረሃብ ማለቁ ገሃድ ሆኗል። እንዳይተነፍስና እንዳይናገር አፍነው የለጎሙት፣ ያሰሩት፣ ያጋዙት፣ የገደሉትና ተስፋውን ያጨለሙበት በሰማንያ ሚሊዮኖች የሚቆጠር ህዝብ በቃ ለማለት የቀረው አንድ ሃሙስ ብቻ መሆኑ እየታየ ነው።

የወያኔ ዘረኛ ጉጅሌ እንደነሙባረክ እንደነጋዳፊ ለግዚያዊ መደበቂያነት እንኳን የሚያገለግለው ሃገራዊና ማህበረሰባዊ ከባቢያዊ መሰረት የሌለው፣ ከሃገር ክህደት አንስቶ፣ በሁሉም የሃገሪቱ ዜጎች ላይ አፈናና ድህነት አምራች በመሆን የሚጠየቅ በመላው ህዝብ ፊት እርቃኑን የቆመ የጥቂት ዘራፊዎች ቡድን መሆኑ ታውቋል። የገዥ ጉጅሌው ጭምብሎቹ ሁሉ ወልቀው፣ ማጭበርበሪያ ስልቶቹ አልቀው፣ በቅጥፈት ሆነ በጉልበት እድሜውን ማስረዘም የሚችልበት እድል እየጠበበበት የመጣ ቡድን ሆኗል። የሰሞኑን የወያኔን የያዙኝ ልቀቁኝ መፈራገጥ፣ ከጣረ ሞት መፈራገጥ ለይተን ልናየው አይገባም።

የወቅቱ የህዝብ ወገኖች ስራ ወያኔ በሃያ የግፍ አገዛዙ ዘመናት ያላሳየን ደግነት ለዚህ ዘረኛ ጉጅሌ በማሳየት የዚህን ባለጌ ስርአት የስቃይ እድሜ ማሳጠር ብቻ ነው። የሰሞኑ ተረኛ "አሸባሪ" ታሳሪዎች ለህዝብ ወገኖች እንድንፈታ ታገሉልን የሚል ጥያቄ የላቸዉም። ከመታሰራቸዉ በፊት ይህ እንዲመጣ ጠንቅቀዉ እያወቁ የገቡበት ጉዳይ ነዉና። ይልቁንስ የእነርሱም ሆነ የህዝቡ ጥያቄ በመካከለኛው ምስራቅና በሰሜን አፍሪካ የህዝብ ወገኖች በተግባር እንዳስመሰከሩት ሁሉ ትግሉ ቀናትና ወራት ሊጠይቅ የሚችል እልህ አስጨራሽ ቢሆን እንኳዋን ያለመታከት በፅናት በመላዉ አገሪቱ እንዲፋፋምና የአገዛዙን ፍፃሜ ማፋጠን እንዲቻል ሁሉም በየአቅጣጫዉ የሚጠበቅበትን ለማድረግ ዝግጁነቱን በተግባር ማሳየቱ ላይ ነዉ።

**ውድመት ለዘረኛው የወያኔ ጉጅሌ!**
**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!**

PR@ginbot7.org

## ከራሱ በቀር በጀሌዎቹ ላይ እምነት የሌለው ህወሃት በብአዴን አመራር . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

የፈለጉ የብአዴን አባልን በስልክ አናግሮ ባገኘው መረጃ እንደገለጸው ለህዋሃት ወያኔ ይህን ያህል ዘመን በግብዝነት አይኔን ጨፍኘ እንደከብት ስነዳ መቆየቴ እጅግ ያንገበግበኛል፤ ለወያኔ ማደሬ ያተረፈልኝ ነገር ቢኖር በከፍተኛ ደረጃ በህዝብ መጠላትን ነው፣ እናም ሞያ በልብ እንዲሉ ምን ማድረግ እንዳለብኝ የማውቅ እኔው ነኝ፣ በማለት መግለጻቸውን ለመረድት ችለናል።

ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ የተለያዩ ብሄረሰቦች አባላትን በተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች በመደለል የሚፈልገውን ሁሉ በማስፈጸም ላይ እንደሚገኝ በተደጋጋሚ ሲዘገብ የቆየ ቢሆንም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየከፋ በመጣው የጉሮ ውድነት ምክንያት ደጋፊ ተብዬዎች እየተከፋፈሉ መምጣታቸውንና አብዛኞቹ ልባቸው እንደሸፈተ ለማወቅ ተችሎአል።

## ከዓለምአቀፍ የሲቪልና ፖለቲካዊ ንቅናቄ ለዴሞክራሲያዊ ለውጥ በኢትዮጵያ በሕወሀት/ኢህአዴግ ወቅታዊና ስር የሰደደ ጭቆና ላይ የወጣ አስቸኳይ የጋራ መግለጫ

*ዕሁድ፡ መስከረም 7/2004 (9/18/2011)*

**የኢትዮጵያ ሕዝብ የስልጣን ባለቤት ይሆናል !!**

በሰሜን አሜሪካ የምንኖር፡ እና በኢትዮጵያ ለውጥ እንዲመጣ የምንታገል፡ የፖለቲካ ድርጅቶችና የሲቪል ማህበራት አባላትና ድጋፍ ሰጪ ማህበራት፡ ሰሞኑን የሕወሀት/ኢህአዴግ አፋኝ አገዛዝ፡ በጋዜጠኞች፡ የፖለቲካ መሪዎች እና የጥበብ ሰዎች ላይ እየወሰደ ያለውን የእመቃ እርምጃ በተመለከተ በ **"በቃ ንቅናቄ"** የተዘጋጀ ለሰዓታት የዘለቀ፡ አስቸኳይ ስበሰባ አድርገን፤

የህወሀት/ኢህአዴግ የአዲስ ዓመት አዲስ ዙር እስራትን ስረ-መሰረት ተረድተን፤ የአረቡ ዓለም አመጽ ወደአፍሪካና ኢትዮጵያ በሚያደርገው መስፋፋት መሸበሩንና የ**"ጸረ-ሽብር ህጉ"**ም ሽብርን ለመዋጋት ሳይሆን፡ ማናቸውንም የህሳብ ልዩነት ለማጥፋትና የነጻነት ታጋዮችን ለመወንጀል እንደሆነ ተገንዝበን፤

አገዛዙ ከሚለፍፈው የድርብ ቁጥር የምጣኔ-ሀብት እድገት በተቃራኒ በከፍተኛ ስራ-አጥነት፤በትምህረት ጥራት ጉድለት፣ ስር በሰደደ የከተማና የገጠር ድህነት፣ በዋጋ ግሽበት፣ በንጹህ ውሀ እጦት፣ በሙስና መንሰራፋት፣ በዜጎች ለዘመናት ከኖሩበት መሬት መፈናቀል፣ በተስፋፋው ረሀብና ድርቅ፡ እንዲሁም በጥቂቶች የስርአቱ ደጋፊዎች ብልጽግናና በብዙዎች መደህየት ተቆርቁረን፡

ጎሳን መሰረት ያደረገው የሕወሀት/ኢህአዴግ ማፊያና ቅጥረኛ ቡድን፡ በኢትዮጵያ ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ መልኩ፡ ገበሬዎችን ለዘመናት ከኖሩበት መሬት እያፈነቀለ፡ የከተማ መሬቶችንም ለራሱ እና የኔ ለሚላቸው የድርጅት አባላት በሚያደርገው እደላ ተቆጭተን፤

ከሀያ አመታት አገዛዝ በኋላም፡ በኢትዮጵያ በሚታየው አስደንጋጭ ድርቅና ረሀብ አዝነን፡ በተቃራኒው የህወሀት አገዛዝ በደቡብና በምስራቅ ኢትዮጵያ አካባቢ ያለውን መጠነ-ሰፊ ረሀብና ግጭት ለመሸሸግ በሚያደርገው ጥረት፣ ይባስ ብሎም አለምአቀፍና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እንዳይታዘቡ፣ የአገር ውስጥም ሆነ የውጭም ጋዜጠኞች እንዳይዘግቡት በሚያደርገው እገዳ እና ይሄንን ለመዘገብ በተጓዙት ሁለት የስዊድን ጋዜጠኞች ላይ ባደረሰው ጉዳትና እስራት ተቆጥተን፤

የሕወሀት/ኢህአዴግ ስርአት አያሌ የሰብአዊ መብት ጥሰትና መንግስታዊ ሽብርተኝነት እየፈጸመ፣ የውጭ እርዳታንም ለፖለቲካ ጭቆና እያዋለ ስለመሆኑ የሚያሳይ ጠንካራ ማስረጃ በተያዘበት በአሁኑ ወቅት አሜሪካንን ጨምሮ፡ የአውሮፓ ህብረትና ሌሎችም ምእራባዊያን መንግስታት ይሄንን ማስረጃ ችላ ብለው፡ ለሕወሀት/ኢህአዴግ አገዛዝ በሚሰጡት የገንዘብ እርዳታ በማዘን፡

የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ በ2004 የአዲስ አመት መልእክት፡ ህዝቡ ለትግል እንዲነሳና የተነጠቀውን ነጻነት እንዲያስመልስ ያቀረበው የትግል ጥሪ በዋነኛዎቹ የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች ተቀባይነት ማግኘቱን ተገንዝበን፤

በአዲስ አበባ ለመስከረም 21/ 2004 የተጠራውን የተቃውሞ ሰልፍ ጥሪ ወቅታዊነት አድንቀንና የሕወሀት አፋኝ አገዛዝም የሰልፍ ፈቃድ መከልከሉ በሰሜን አፍሪካና በመካከለኛው ምስራቅ የተቀጣጠለው ሕዝባዊ አብዮት፡ ወደ ኢትዮጵያም እየተስፋፋ መሆኑን እንደሚጠቁም አጢነን፣

ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ከተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች ትብብር ጋር በተያያዘ የሚደረገውን እንካ ሰላንቲያ አላስፈላጊነት ተረድተንና ይህም ከደጃፋችን የደረሰውን አብዮት ለማስኬድ እንደማይጠቅም አስተውለን፣የሕወሀትን ጎሳ-ተኮር አምባገነን አገዛዝ ለመጣል የሚደረገው ትግል የሁሉንም የፖለቲካ፣ሲቪልና ማህበራዊ ሀይሎች እጅ ለእጅ ተያይዞ መስራት አስፈላጊነትን አጽንኦት ሰጥተን፡

የሚከተሉትን ውሳኔዎች አስተላልፈናል፡

1. የአንድነት ለፍትህና ዴሞክራሲ ፓርቲ፡ በ2004 የአዲስ አመት መልእክቱ፡ የኢትዮጵያ ህዝብ ልክ እንደ 1966ቱ አብዮት፡ የፖለቲካ ድርጅቶች እስኪቀሰቅሱት ሳይጠብቅ፡ የተነጠቀውን ነጻነት ለማስመለስ ባንድነት እንዲነሳ ያቀረበውን የትግል ጥሪ ሙሉ በሙሉ አጽድቀናል።
2. በአዲስ አበባና በሌሎችም ከተሞች ለመስከረም 21 የተጠራውንና ወደፊትም የሚጠራውን የተቃውሞ ሰልፍ ሙሉ በሙሉ ደግፈን፡ ኢትዮጵያዊያን በሚኖሩባቸው ዋና ዋና የሰሜን አሜሪካና የአውሮፓ ከተሞችም ተመሳሳይ የተቃውሞ ሰልፎችን ለማድረግ ወስነናል።
3. በአገር ውስጥም ከአገር ውጪም ያሉ ኢትዮጵያዊያን፡ የህወሀት/ኢህአዴግን አመራርና ቅጥረኛ አባላት እንዲያገሉ ጥሪ እያቀረብን፡ በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያንም፡ የህወሀት/ኢህአዴግ ኤምባሲን አገልግሎት እንዲተዉ፤ ከሕወሀት ጋር የተዛመዱ የንግድ ድርጅቶችን፡ የአምልኮ ቦታዎችን፡ ማህበራትና ተቋማት መገልገል እንዲያቆሙም ጥሪ እናቀርባለን።
4. የአሜሪካና የካናዳ መንግስታት፡ ከህወሀት/ኢህአዴግ አምባገነንና ህገ-ወጥ አገዛዝ ጋር ያላቸውን የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ እንዲቀይሩና፤ የሕወሀት አገዛዝ ጋሻ ጃግሬዎች በሰሜን አሜሪካ ያላቸውን የህዝብን ነጻነት የሚያውክ እንቅስቃሴ እንዲገድቡ ጥሪ እያቀረብን፤ የህወሀት ዘረኛ አመራሮች፡ መለስ ዜናዊ፡ በረከት ስምኦን፡ ሽመልስ ከማል፡ ዲና ሙፍቲ፡ ሬድዋን ሁሴን፡ ሀይለማሪያም ደሳለኝ፡ ስዩም መስፍን፡ አዜብ መስፍን፡ ሳሞራ የኑስ፡ ጌታቸው አሰፋ፡ አዲሱ ለገሰ፡ ብርሀነ ገብረክርስቶስና፡ ስብሀት ነጋ፡ በዘር ማጥፋት ወንጀልና ሰቆቃ በመፈጸም፡ በአለምአቀፉ የወንጀል ፍርድቤት ሊያቆማቸው የሚችል ጠንካራ ማስረጃ ስላል፡ ማናቸውንም የቪዛና ኮንሱላር አግልግሎት እንዲከለክሉ እንጠይቃለን።
5. የአቶ አልባና ሌሊሳ፡ በቀለ ገርባ፡ ደበበ እሸቱ፡ አንዱአለም አራጌ፡ ዘመኑ ሞላ፡ ናትናኤል መኮንን፡ እስክንድር ነጋ፡ ርእዮት አለሙ፡ ውብሸት ታዬ፣ስለሺ ሃጎስ ሌሎችም የሕወሀት/ኢህአዴግ እስር ቤቶችን ያጣበቡትን የፖለቲካ እስረኞች እስራት አጥብቀን እያወገዝን፤ እነዚህ የጥበብ፡ የፖለቲካና ሰላማዊ ሰዎች የታሰሩበት ምክንያት የሀሰት፤ የታሰሩበት ህግም ዴሞክራሲን ለማፈን የወጣ አሸባሪና አፋኝ ህግ ስለሆነ፡ ህዝቡ ለዚህ ሕግ እንዳይታዘዝ፡ እስረኞቹም ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲፈቱም እንጠይቃለን። አለምአቀፍ የሰብአዊ ድርጅቶችም እስረኞቹ በእስር ባሉበት ወቅት ምንም አይነት ድብደባና ሰቆቃ እንዳይፈጸምባቸው እንዲጎበኟቸው ጥሪ አቀረብን፤ እኛም የእስረኞቹን ቤተሰቦች በሞራልና በቁሳቁስ ለመርዳት ወስነናል።
6. የሲቪልና የፖለቲካ ድርጅቶችም፡ የተጋረጠባቸውን መሰናክል አስተውለው፡ ባስቸኳይ፡ ሁሉን አቀፍና ሰፊ የኢትዮጵያን የነጻነት ትግል የሚያፋጥን፣ የነጻነት ትግሉን ከግብ የሚያደርስ፡ እንዲሁም አገሪቱን ለብሄራዊ እርቅና ለሰላም፡ ለነጻና ፍትሀዊ ምርጫ የሚያሰናዳ፣ህግና ስርአትን የሚያስጠብቅ፣ የአገሪቱን ፖለቲካዊና ግዛታዊ ሉአላዊነት ወደ ሚያስከብር የአደራ መንግስት የሚወስድ፡ ጊዜያዊ ብሄራዊ ምክር ቤት ወይንም ሸንጎ (National Council) እንዲያቋቁሙ ጥሪ እናቀርባለን።
7. ባደረግነው ስብሰባም፡ በኢትዮጵያ ውስጥ ለነጻነት፡ ለፍትህና ለሕግ የበላይነት ለሚደረገው ትግል የማያወላዳ እገዛ ለማድረግ ቁርጠኝተነታችንን አድሰን፤ ይሄንንም ከግብ ለማድረስ ዓለም-አቀፍና መጠነ-ሰፊ የዲፕሎማሲ፣ የቁሳቁስ፣ የህሳብና የሞራል ዘመቻ ለማድረግ በአንድነት ወስነናል። የህወሀትን ዘረኛ አስተዳደር፡ ሰላምን፣ብልጽግናንና ነጻነትንነ በሚያመጣ ዴሞክራሲአዊ መንግስት ለመተካት በሚደረገው ትግል ላይ፡ ሁሉም የዴሞክራሲ ሀይሎች እንዲተባበሩም፡ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

የኢትዮጵያ ሕዝብ የስልጣን ባለቤት ይሆናል !! ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!

ለበለጠ መረጃ: Ethiopians.say.beka@gmail.com

## ዘረኛው ወያኔ በአዲስ አበባ ትምህርት ያቋረጡ ወጣቶችንና ጎልማሶችን ሥልጠና እና ብድር እሰጣችኋለው በሚል ሰበብ በየመንደሩ መቀስቀሳና መመዝገባ እንደጀመረ ተዘገበ

የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ወያኔን በሚቃወም ምንም አይነት እንቅስቃሴ እንዳይሳተፉ ለማድረግ በየመንደሩ ከፍተኛ የሆነ የሕዝብ ንቅናቄን ለመፍጠር የሚያስችል የቅስቀሳ ሥራ በወያኔ ካድሬዎች መሠራት መጀመሩን የአዲስ አበባ ወያኔ ኢህአዴግ ጽ/ቤት የዜና ምንጮቹን በመጥቀስ የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት ዘገበ።

ኢሳት ምንጮቹን በመጥቀስ እንደዘገበው ይህ አዲስ የተጀመረው ዘመቻ የህብረተሰቡን ደካማ ጎኖች በመለየት ማህበረሰቡን ማሰባሰብና በወያኔ ኢህአዴግ መርሃ ግብር ተሳትፎ እንዲያደርጉ ማነቃነቅ የሚል ዋና ዓላማ አለው ተብሉአል፡፡ ይህን መሰሪ አላማውን ከግብ ለማድረስ በየመሥሪያ ቤቶች የሚገኙ የዘረኛው አገዛዝ ፓርቲ ዓባላትና ካድሬዎች በመሠረታዊ ድርጅታቸው መዋቅር በኩል በመሥሪያቤታቸው እንዲሰሩ ጥብቅ መመሪያ የተሰጣቸው ሲሆን፣ በየመንደሩና በየአካባቢው ግን እንደማህበረሰቡ ሁኔታ በሴቶች ሊግ፣ በወጣቶች ማህበራትና ሊግ፣ በአነስተኛና ጥቃቅን እና መሰል የወያኔ ፍልፈል ማህበራት በኩል እንደሚከናወንም ተያይዞ የደረሰው ዘገባ አመልክቱአል፡፡

በሌላም በኩል በተያያዘ ዘገባ የወያኔው ኢህአዴግ አገዛዝ ካያዝነው ሣምንት ጀምሮ በየቀበሌውና በየወረዳው ጽ/ቤት የወታደር ምልመላ መጀመሩን በየአካባቢው ላይ በለጠፈው የሥራ ማስታወቂያ የገለጸ ሲሆን የውስጥ ለውስጥ ቅስቀሳም መጀመሩ ታውቁአል፡፡

እንደ ኢሳት ዘገባ ሪፖርተሮቹ ተዘዋውረው በተመለከቱዋቸው የአራዳ፣ የኮልፌ ቀራኒዮ፣ የአዲስ ከተማ፣ የጉለሌና የንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተሞች መንደሮች የተለጠፈው የወታደር ምልመላ ማስታወቂያ የሀገር መከላከያ ሚንስቴር መሥሪያ ቤት ማህተም ያለበት ሲሆን፣ ማስታወቂያው በወታደርነት ለመቀጠር የፈለገ ሰው በመጀመሪያ በብሄር ብሄረሰቦች መብት የሚያምን፣ ሕገመንግሥቱን የተቀበለ፣ እድሜው ከ18 እስከ 22 ዓመት የሆነው፣ ከቀበሌውና ከፖሊስ የድጋፍ ደብዳቤ ማቅረብ የሚችል፣ ያላገባና እስከ ስምንተኛ ክፍል የተማረ ወይም እየተማረ ያለ መሆን አለበት የሚል መስፈረት ማስቀመጡ ታውቁአል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**መካከኛ ሞገድ**:- በ 358 MB, በ 837 kHz

**አጭር ሞገድ**:- በ 31 MB በ 9700 KHz

በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz

በ 49 MB በ 5980 KHz

እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:00 እስከ 2:30 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን። **ማሳሰቢያ**:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org